4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

ቀን፡ የካቲት ፲፰ ቀን ፪ ሺህ ፪ ዓ.ም.
ቁ. 302/2010

*«ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር» መዝ ፻፲፭፡፮*
*«የቅዱሳኑ ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው» መዝ 115፣6*

በቅድሚያ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን።

የብፁዕ አባታችን የአቡነ ዜና ማርቆስ ሊቀ ጳጳስ ዕረፍት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ኃዘን ነው። ብፁዕነታቸው መላ ዘመናቸውን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የምትገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅንነትና በታማኝነት በማገልገል ሐዋርያዊ ግዴታቸውን በብቃት የተወጡ ፤ በተለይም በስደት ሀገር የሚገኘውን ሕዝበ ክርስቲያን በሃይማኖቱ እንዲፀናና በኢትዮጵያዊነቱ እንዲኮራ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላኩ በሁሉም ዘንድ ተወዳጅ አባት ነበሩ።

የብፁዕነታቸው ዕረፍት በእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆንም ፤ ሕያው ስለሆኑ በትጋት ያገለገሉትን አምላካቸውን አሁንም ከመላእክትና ከቅዱሳን ጋራ በሰማይ እያመሰገኑት እንደሆነ እናምናለን። ይሁን እንጂ በአካለ ሥጋ ከእኛ መለየታቸው አሳዝኖናል።

ቅዱስ ሲኖዶስ የብፁዕነታቸውን ጸሎተ ፍትሐት እና ሥርዓተ ቀብር በሲያትል መካነ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል እንደሚፈጸም ያወጣውን መርሃ ግብር አክብራችሁ የቤተ ክርስቲያናችሁን ተወካይ እንዲገኙ በማድረግ ፣ የኃዘን መግለጫ ደብዳቤዎችን በመላክ ፣ አበባና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን በመስጠት ፣በቀትታ በድህረ ገጽ ፣ በቴሌቭዥን ፣ በራድዮ ፣ በጋዜጣና በተለያዩ ዘዴዎች እንዲሰራጭ በማድረግ ለብፁዕነታቸው ያላችሁን ልባዊ ፍቅር ስለገለጻችሁ ቅዱስ ሲኖዶስ ምስጋናውን ያቀርባል። የብፁዕነታቸው በረከትና ረድኤት ከሚወዷችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ጋር ይሁን።

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ

ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የኔቫዳ አሪዞናና አይዳሆ ኤጲስ
ቆጶስ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ ቅዱስ ሲኖዶስ ምክትል ዋና ጸሐፊ
Aba Yoseph Bishop of Nevada,
Arizona, Idaho & the exiled
E.O.T.C Holy Synod vice secretary